**ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ**

**የ8ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና**

**አማርኛ 2016 ዓ.ም/2024 G.c**

**የጥያቄ ብዛት 60** **የተፈቀደው ሰአት 1 ሰአት**

**አጠቃላይ ትእዛዝ**

ይህ የአማረኛ ቋንቋ ፈተና ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 60 ጥያቄዎች ተካተዋል ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሠጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡ በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መሥራት ይጠበቅባቹሀል፡፡መልስ የሚሠጠው ከፈተና ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው፤ በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መፅዳት አለበት፡፡

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው 1 ሰአት ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰአት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናውን መስራት ማቆም አለብን፡፡ ፈተናው እንዴት እንደሚሠበሠብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገረን ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን፡፡

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም ፤ ፈተናውን እንዳይፈተን ይደረጋል፡፡

ፈተናውን መሥራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት፡፡

**ፈተናውን መሥራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድለትም !**

\ክፍል አንድ

**<u>መመሪያ አንድ ፦ ከጥያቄ 1 እስከ 5 ድረስ የቀረቡትን ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሠጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።</u>**

**<u>ምንባብ</u>**

በሀገራችን <<እድሜ መስታወት ነው>> የሚል የቆየ አነጋገር አለ ። በልደትና በሞት መካከል መጀመሪያ ህጻንነት፣ ከዚያ ጉርምስና፣ ወጣትነት፣አዋቂነት፣ሽምግልና፣እርጅና፣ ሁሉም በየተራ ወቅቱን እየጠበቀ ይመጣል ከህጻንነት እስከ ጉርምስና ያለው ወቅት ወይም የልጅነት ክፍል ዘመን በየአጋጣሚው የሚታወስ ፣ እንደ ገጠመኙ ብዛትና ማነሱ ጥሩነትና መጥፎነት እንደትዝታው ጥራትና ደብዛዛነት ፣የሚናፈቅ ወይም የሚዘገንን ሊሆን ይችላል። አሳዳጊ ወይም የወላጅ ፍቅርን አግኝቶ በተስማሚ አካባቢ ከሚወዱትና ከሚግባቡት ባልነጀራ ጋር ማደግ ፣ ሲነጋ መቦረቅ ጀንበሯ ስታዘቀዝቅ ገና ደንገዝገዝ ሲል እቤት መከተት ሳያሥቡ ሳይጨነቁ መተኛት ወፍ ሳይንጫጫ መነሳት እንደገና ቡረቃ ----- ይህን ይህን ሲያስቡት መልካም ትዝታው ከልብ አይጠፋም በችግርና በመንገላታት፣ በብቸኝነትና ጭቆና ፣ በህመምና ጉስቁልና ማደግ ደግም የዚህ ተቃራኒ ሊሆን ይችላል።

ወደ አዋቂነት የሚያሸጋግረው የወጣትነት ዘመን ጉርምስና በመጠኑ የሚቀላቅል ይሁን እንጂ << ከሰርክ ሰርክ >> ጨዋታ በደረጃው ከፍ ያለ የህልም ዓለም አይነት ምኞት እውነተኛ መልኩን የሚያገኝበት የተስፋ ቡቃያ የሚሸትበት ልበ ሙሉነት ገና የሚታይበት የአእምሮ የጉልበት ሀይል የሚጋጋልበት ወቅት ነው። ቤተሰብ ለመመስረት ዓላማን በተግባር ለመተርጎም ይዘጋጁበታል አካባቢን በሚገባ ማወቅ በጎውን ከክፉ መለየት ይጀምርበታል የሀገርን የወገንን ፍቅር ይጎላበታል።

ከእዚህ በኋላ ያሉት ወቅቶች መጃጀት እስኪመጣ ድረስ ቤተሰብና የማህበረሰብ ኃላፊነት አመዛዛኝነት፣ ትእግስትና እርጋታ የሚታይባቸው እውቀት የሚዳብርባቸውና ብስለት የሚገባቸው ናቸው እዚህ ላይ በጣም የሚገርመው የመጃጀት አጭር ወቅት ድንገት ሲመጣ ከአመት አመት እየተካበ ተከምሮ የኖረው ሁሉ በአእምሮ ሚዛን መቃወስ በአንዴ ፈርሶ ወደ ህጻንነት የመመለሱ ነገር ነው። መቼም በዚህ ጊዜ እድሜ መሥታወት መሆኑ ይቀርና ጭቃ ማቡኪያ ይሆናል እንዲህም ሲሆን የሠው ልጅ በህጻንነቱ ልዩ መአዛ ሠጥታ ከማቆንጀት አልፎ ተርፎ የአህያ ውርንጪ የምታሣምረው ተፈጥሮ በገዛ ስራዋ ላይ አስቀያሚ ሣቋን መሣቅ ትጀምራለች።

ምንጭ ፡-መሥፍን ሀብተማርያም <<የቡና ቤት ስእሎች>>

1.በምንባቡ መሠረት <<እድሜ መስታወት ነው>> የሚለውን የቆየ አነጋገር የሚያስረዳን የቱ ነው።

A. እድሜ እንደመስታወት ማለት ነው B .የእድሜ መሥታወትነት እያደረ ይታወቃል ማለት ነው

C. ብዙ እድሜ ያለው ሁሉ ብዙ ያውቃል ማለት ነው D. በእድሜ መሠንበት ክፉውንም ደጉንም ለማወቅ ይረዳል

ማለት ነው

2. ከህጻንነት እስከ ጉርምስና ያለው ወቅት እንደአጋጣሚው ጥሩና መጥፎነት ምን ሊሆን ይችላል።

A. የሚያስደስት ወቅት ብቻ ሊሆን ይችላል። B. የሚያሳዝን ወቅት ብቻ ሊሆን ይችላል።

C. ሀዘን ደስታ የሚፈራረቅባቸው ወቅቶች ሊሆኑ ይችላሉ። D. ሁሉም መልስ ነው።

3 .ጀንበሯ ሳታዘቀዝቅ ገና ደንገዝገዝ ሲል ማለት ምን ማለት ነው?

A. ለአይን ሲይዝ ማለት ነው። B. ጨለማ ሲሆን ማለት ነው።

C. ጸሀይ አልጠለቀችም ማለት ነው። D. ሀ እና ሐ መልስ ነው።

4 በምንባቡ መሠረት "ወፍ ሲንጫጫ" ማለት ምን ማለት ነው?

A. ወፍ ሲጮህ ማለት ነው ። B. ወፎች እየበረሩ ሲጮሁ ማለት ነው ።

C. ሲነጋጋ ማለት ነው። D. ሲጨልም ማለት ነው።

5 ."የተስፋ ቡቃያ የሚሸትበት" የሚለው አባባል ምን ማለት ነው?

A. ቡቃያ በመሬት ላይ የሚታይበት ወቅት ነው። B ተስፋ ያደረገው ነገር ትክክለኛ መልኩን የሚያሣይበት ወቅት ማለት ነው C ቡቃያ እሸት የሚሆንበት ወቅት ማለት ነው። D እሸት የሚበላበት ወቅት ማለት ነው።

**<u>መመሪያ ሁለት ፡- ከጥያቄ 6 እስከ 60 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ</u>**

6. መንገዱን <u>እያሣበርን</u> ከቦታው ደረስን የተሠመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ _______ነው።

A እያካለልን B እያረፍን C እያዘገምን D እያቋረጥን

7. ቧልት ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺ ____________ነው።

A ቀልድ B ቦዘኔ C ቁም ነገር D ስራ ፈት

8. ሲበሉ የላኩት ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ተቃራኒ ፍቺው ___________ነው።

A የማያዳምጥ B ነብራራ C ደረቅ D ሀእና ለ መልስ ነው።

9. "ቀጨማ" ለሚለው ቃል ተመሣሣይ ፍቺው ___________ነው።

A የማር ገፈት B ምኞት C ከብት ጠባቂ D ለመፋቂያ የሚያገለግል ተክል

10. አንቀጾች በቢጋር ስርአት ባለው መልኩ ተቀናጅተው ___________ የሚፈጥሩበት ጥበብ ነው።

A ሀረግ B አንቀጽ C አረፍተ ነገር D ድርሰት

11. ከሚከተሉት ውስጥ የራሡ መመሪያ የሌለው _________የቱ ነው።

A ንግግር B ስነ ቃል C ክርክር D ውይይት

12. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የንግግር አዘገጃጀት መመሪያ አይደለም ።

A የንግግር ርእስ መምረጥ። B አድማጮችን በሚያረካ መልኩ ንግግር ማድረግ ።

C የንግግሩን አላማ በግልጽ መረዳት። D የንግግር ርእስ መወሰን ወይም ማጥበብ።

13. በሞሰቡ ሙሉ ይቅረብ እንጀራው

አስተዳዳሪያችን ሆደ ሰፊ ነው

ከላይ የቀረበው ቅኔ ህብረቃሉ የትኛው __________ነው።

A ይቅረብ እንጀራ B አስተዳዳሪያችን C ሆደ ሰፊ D ሰፊ ነው

14. ከላይ የቀረበው ቅኔ የሠም ፍቺ ከቀረቡት አማራጮች የትኛው ነው?

A ሆደ ሰፊ B አስተዳዳሪያችን ታጋሽ ነው። C ቻይ ነው D አስተዳዳሪያችን ሆዳም ነው።

15. ከላይ የቀረበው ቅኔ የወርቅ ፍቺ ከቀረቡት አማራጮች የቱ ነው?

A አስተዳዳሪያችን ሆዳም ነው። B ሆደ ሰፊ

C አስተዳዳሪያችን ሆደ ሰፊ ነው D ይቅረብ እንጀራው

16. "ላም" የሚለው ቃል የትኛውን አብዢ ቅጥያ ይወስዳል?

A - ዎች B - ኦች C - ኣት D - ኢት

17. "ካህን" የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ሲጻፍ __________ ይሆናል።

A ካህናት B ካህኖች C ካህናቶች D ሁሉም መልስ ነው

18. ተማሪዎች ለፈተና ተዘጋጅተዋል ። ይህ አረፍተ ነገር በየትኛው ጊዜ ላይ የተፈጸመ ነው?

A የሀላፊ ጊዜ B የአሁን ጊዜ C የትንቢት ጊዜ D መልስ አልተሰጠም

19. የኃላፊ ጊዜን የሚያሣየው አረፍተ ነገር የትኛው ነው።

A እህቴ እንጨት እየፈለጠች ነው። B ወንድሜ ነገ ወደ ሀረር ይሔዳል።

C ጦርነቱ ብዙ ንብረት አውድሟል። D ህመምተኛው ወተት ይጠጣል።

20. ከሚከተሉት ውስጥ የትንቢት ጊዜ አመልካች የሆነው የቱ ነው?

A ስለ ሰራን B ሰራን C እንሰራለን D እየሠራን ነው

21. ከሚከተሉት አንዱፐየተለየ ነው።

A ነጠላ B ሌጣ C ጥንድ D ብቸኛ

22. ቡሄ በሉ ግጥም በአንድ ስንኝ ስንት ቀለሞች አሉት?

A አስራ ሁለት B አስር C ስምንት D አራት

23. ሠንጎ መገን ግጥም በሀረጋት _________ ቀለሞች አሉት?

A አምስት B አራት C ስድስት D አስር

24. ከሚከተሉት ድርብ ቃል ያልሆነው የቱ ነው?

A መሠረተ ትምህርት B አይን አፋር C መጥፎ ባህሪ D እግረ ደረቅ

25 .ከሚከተሉት ውስጥ ድርብ ቃል ያልሆነው የቱ ነው?

A ሞኛ ሞኝ B ጅላ ጅል C ትላትል D ምንጣፍ

26. በክርክርና በጭውውት ወቅት የትኞቹን የቋንቋ ክሂል እናዳብራለን?

A መጻፍና መናገር B ማንበብና ማዳመጥ C መናገርና ማዳመጥ D ማንበብና መጻፍ

27 .ከሚከተሉት ሀሣቦች ስለውይይት አቀራረብ መመሪያ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

A በተቻለ መጠን ተደራሢያንን ማርካት B ውይይቱን በተወሰነ ጊዜ ገደብ እንዲያበቃ አለማድረግ

C የውይይቱን ርእስ ማሥተዋወቅ D ተደራሢያን በጥሞና ስላዳመጡን ማመስገን

28. ከሚከተሉት የትኩረት ነጥቦች መካከል ስለ ንግግር አቀራረብ መመሪያ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

A አካላዊ እንቅስቃሤ የተለያዩ አገላለጾችን መጠቀም B ተደራሢያንን በንግግር ወቅት በአይን አለመቃኘት C እኔ ብቻ ልደመጥ ብሎ ማሠብ D የተደራሢያንን ስሜትና ፍላጎት መገደብ

29 .ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ከቀረቡት ርእሶች አመዛዛኝ ድርሰት የሚያሥችለው የትኛው ነው።

A የጦርነት ሜዳ ውሎ ታሪክ B ኮሌጆችና የ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

C የስዜጋ ትምህርት D የማረሳው ቀን ትዝታ

አጼ ሚኒሊክ ከ ነሀሤ 13/1835 ዓ.ም በአንኮበር ከሸዋው ንጉስ ኃይለመለኮትና ወ/ሮ እጅግ አየሁ ተወለዱ።

30. ከላይ የተጻፈው በየትኛው የድርሰት አጻጻፍ ስልት ነው?

A ስእላዊ ድርሰት B አመዛዛኝ ድርሰት C ተራኪ ድርሰት D ገላጭ ድርሰት

ቤተ መጻህፍትን መጠቀም የሚፈልግ ሰው ፤ በመጀመሪያ የመጽሀፉን ርእስና የደራሢውን ስም ይዞ የመጻህፍት ማውጫ ካርዶች ወደ ተቀመጡበት ሳጥን ይሔዳል።

31. ከላይ የተጻፈው ጽሁፍ በየትኛው የድርሰት አይነት ነው?

A አመዛዛኝ B ተራኪ ድርሰት C ሥእላዊ ድርሰት D ገላጭ ድርሰት

32. በተፈጸሙ ነገሮች ላይ ተመርኩዘን ውበት ባለው ቋንቋ የሚቀርቡ ጽሁፎች __________በመባል ይታወቃሉ።

A ኢ- ልቦለድ B ልቦለድ C ረጅሕ ልቦለድ D አጭር ልቦለድ

1 አላገኙም ነበር የሚያሥታርቅ ሰው

2 አሁን ግን ሁለቱ መሀንዲሥ መርጠው

3 እሳትና ውሀ ሢጣሉ ኖረው

4 ለአለም ሊያበሩ ነው እሳት ልጅ ወልደው

33. ከላይ የቀረበው ግጥም ተዘበራርቆ የተቀመጠ ሢሆን ተስተካክሎ ሢቀመጥ ___________ ይሆናል።

A 3፣1፣2፣4 B 3፣2፣1፣4 C 2፣1፣3፣4 D 2፣3፣1፣4

34 .ጊዜው ቀረብ ሲል አመት በአል ሲመጣ

የስጋ ከብት ሁሉ ___________ ይህንን ግጥም ሊያሟላ የሚችለው ሀረግ የቱ ነው?

A ከቤት አይውጣ B ከያለበት ወጣ C ከየትም አይመጣ D ከወዴት ላምጣ

35 .___________ እርፍ ያልነቀነቀ

በሀምሌ መባቻ ተጣጥፎ ወደቀ ። ይህንን ግጥም ሊያሟላ የሚችለው ሀረግ

A ትጉህ ገበሬ B ሰነፉ ገበሬ C ጎበዙ ገበሬ D ታታሪ ገበሬ

36. "ሰዎች" የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያ __________ ነው።

A - ዎች B - ኦች C - አማ D - ነት

37. አጭር ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ የሚለይባቸው ባህሪያት ውስጥ የማይመደበው

A ጥድፊያ B ትልም C ነጠላ ውጤት D ቁጥብነት

38. በውሀው መበከል ምክንያት ህጻናቱ ታመሙ ። ይህ አረፍተ ነገር ከልቦለድ አላባውያን የትኛውን ያመለክታል?

A ታሪክ B ግጭት C ትልም D ጭብጥ

39. ሢጋራ የሚያጨስ ፣ ጫት የሚቅም፣ ቁማር የሚጫወት ሰው ፤ የሣንባ ህመም ፣ የማህበራዊ ግንኙነት መቃወስ፣ የኢኮኖሚ ውድቀት ያጋጥመዋል። ይህ አረፍተ ነገር በውስጡ

A ብዙ ምክንያት ብዙ ውጤትን ያሣያል B ብዙ ምክንያት ነጠላ ውጤትን ያሣያል

C ነጠላ ምክንያትና ብዙ ውጤት D ነጠላ ምክንያት ነጠላ ውጤት

40. የዛሬ ሰው ሀብ ሀብ ማለት ይወዳል። የተሠመረበት ፈሊጣዊ ንግግር ፍቺው

A መጣላት B መናቆር C መግደርደር D ካገኘው ሰው ጋር መዋደድ

41. የሀሣብ ተመሣሣይነት ያላቸው አረፍተ ነገሮች ለማያያዝ __________ እንጠቀማለን።

A መሸጋገሪያ ቃላት B ኢ-ተዘውታሪ ቃላት C ድርብ ቃላት D ተዘውታሪ ቃላት

42. ወ/ሮ አምሳል የጠመቁት ወረግቡ በጣም ጣፋጭ ነው ። የተሠመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺው________ነው።

A አረቄ B ጠላ C ለጋ ጠጅ D ኮረፌ

43. አንድን ሁነት ከመነሻው እስከ መድረሻው የሚዳስስ የድርሰት አይነት_________ይባላል።

A ስእላዊ B ተራኪ C አመዛዛኝ D ገላጭ

44 .በእለት ከእለት ኑሯችን ውስጥ የማንገለገልባቸው ቃላት________ይባላሉ።

A ተልሙድ ቃላት B ተዘውታሪ ቃላት C ድርብ ቃላት D ኢ-ተዘውታሪ ቃላት

45. ስለ ሀረግ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

A  ከቃል የሠፋ ከ አ/ነገር ያነሠ ነው። B አንድ ሀረግ አይነቱ የሚወሰነው በ መሪው ነው

C ሁሉም ሀረጎች ቀኝ መሪ ናቸው D ሀ እና ለ መልስ ናቸው

46.ምንዳ <u>በጣም ጎበዝ</u> ተማሪ ነው ። የተሰመረበት ሀረግ ከ __________ ይመደባል።

A  ከቅጽላዊ B ከስማዊ C ከግሳዊ D ከመስተዋድዳዊ

47. ከሚከተሉት አንዱ የተለየ ነው ።

A  ትልቁ ቤት B ነጭ ጃኬት C ዛሬ ገና D ጎበዙ ልጅ

48. ከሚከተሉት የተውኔት አላባውያን የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?

A መድረክ/መቼት B ግጭት C ገጸ ባህሪት D ሁሉም መልስ ነው

49. ከሚከተሉት የሀረግ አይነቶች በመሪው ይለያል

A ግሳዊ ሀረግ B መስተዋድዳዊ ሀረግ C ቅጽላዊ ሀረግ D ስማዊ ሀረግ

50 .አጭር ልቦለድን በሚመለከት የአላባውያንን ምንነት ተምረናል _________ መሸጋገሪያ ቃላትን ወይም ሀረጋትን እንማራለን ። በክፍት ቦታው ላይ በመግባት ክፍት ቦታውን የሚያሟላው ሀረግ የትኛው ነው?

A ይሁን እንጂ B ከዚህ ቀጥሎ C እስከዚ ድረስ D ቢሆንም51.

ሁሉም ኢትዮጵያዊ የድርሻውን በተሠማራበት ሙያ ለሀገሩ እድገት የተቻለውን ማበርከት አለበት።_________ የተሠሩ ስራዎች በቂ ላይሆኑ ይችላሉ ።

A በመቀጠልም B  በመሆኑም C በሌላ ጊዜ D ወደፊት

52. _________የቃላት ቀጥተኛ ወይም መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ነው።

A እማሬአዊ ፍቺ B ፍካሬአዊ ፍቺ C ድብቅ ፍቺ D ሁሉም መልስ ነው

53. እንደ ፍየል ለፍላፊ ናት። ይህ አረፍተ ነገር ____________ነው።

A እማሬአዊ B ፍካሬአዊ C የቤት እንስሳ D መልስ የለም

54. ገቢር ግስን የሚያመለክተው አረፍተ ነገር የቱ ነው ።

A ወንበሩ በአናጺው ተጠገነ B ሌባው በፖሊስ ተደበደበ

C  አህመድ ወረቀት ቀደደ D ወረቀቱ በአህመድ ተቀደደ

55. ከሚከተሉት ግሶች ውስጥ ተገብሮ ግስን የሚያመለክተው የቱ ነው?

A በደለ B ሰራ C ተነዳ D ገደለ

56. በልቦለድ ውስጥ የሚተላለፉ ዋና መልእክቶችን የሚይዝ የልቦለድ አላባ

A ግጭት B ትልም C ጭብጥ D ታሪክ

57. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የቢጋር ጥቅም አይደለም።

A ገጸ ባህሪያትን መወሰን B አላማን ግለጽ ማድረግ

C የሀሣብ ቅንጅትን ማሣየት D መልእክትን ማሥተላለፍ

58. የማንኛውም ቋንቋ መሠረቱ _______________ነው።

A አረፍተ ነገር B ድምፅ C ሀረግ D አንቀፅ

59. የአሁን ጊዜ ግሶች ____________ የሚል ቅጥያን ይጠቀማሉ።

A እየ- እና -አት B አስ- እና -ነው C እየ- እና -ነው D አስ- እና -እየ

60. በጭውውት ውስጥ ሊተገበር የማይገባው የቱ ነው?

A እኔ ብቻ ላውራ ማለት B መከባበር C መደማመጥ D ቀልዶችን ጣል ጣል ማድረግ